# ቅድስና!

የቅድስናን አስተምህሮ በትክክል ለመረዳት፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህን አስተምህሮ አስመልክቶ የተጠቀሱትን ክፍሎች ሁሉ መመልከት ያሻል። ይህን ስናደርግ ማን ተናገረው? ለማን ተናገረው? ስለምንድን ነው የሚናገረው? የተናገረበት ጊዜው መቼ ነው? በክርስቶስ የተፈጸመ የመስቀል ሥራ እንዴት ይታያል? የሚለውን ያገናዘበ መሆን አለበት።

የቅድስና አስተምህሮ ከሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ጋር በትክክል መዛመድ አለበት። ይኼ ማለት የቅድስና አስተምህሮ የሚወክለው እና የሚያብራራው ሁሉ በእግዚአብሔር ዓላማ ውስጥ የራሱ የተወሰነ ሥፍራ እንዳለው እንድንገነዘብ ያደርገናል።

የቅድስና አስተምህሮ በልምድ ሊገለጥ አይችልም። ይኼ ማለት የግል ልምምድ ትንታኔ ቅድስናን በተመለከተ የእግዚአብሔር ቃል የሚሰጠውን ትምህርት ሊተካ አይችልም ማለት ነው።

ቅድስና በግሪክ ቃል ሐጊያሞስ ማለት ሲሆን ቀጥተኛ ፍቺው መለየት ወይም የተለዩ መሆን ማለት ነው። ወደ መጽሐፍ ቅዱስ የቅድስና አስተምህሮ ስናመጣው ለእግዚአብሔር መለየትን  የሚያሳይ ነው።

በብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች፣ ቀናት፣ ቦታዎች ወይም መሬቶች፣ ምግቦች እና ምርቶች ይቀደሱ/ይለዩ ነበር። በአዲስ ኪዳን ዘመን ግን የሚቀደሰው/የሚለየው ሰው ብቻ ነው።

- "ለአምላካቸው (ኤሎሂም) የተቀደሱ ይሁኑ፤ የአምላካቸውንም (ኤሎሂም) ስም አያርክሱ። ለእግዚአብሔር (ያህዌ) በእሳት የሚቀርበውን መሥዋዕት የአምላካቸውን (ኤሎሂም) ምግብ ስለሚያቀርቡ ቅዱሳን ይሁኑ። ካህናት በዝሙት የረከሱትንም ሆነ ከባሎቻቸው የተፋቱትን ሴቶች አያግቡ፤ ለእግዚአብሔር (ያህዌ) የተቀደሱ ናቸውና። የአምላክህን (ኤሎሂም) ምግብ የሚያቀርብ ነውና ቀድሰው፤ እኔ የምቀድሳችሁ እግዚአብሔር (ያህዌ) ቅዱስ ነኝና ቅዱስ ይሁንላችሁ።" (ዘሌዋውያን 21:6-8 NASV)

- "ስድስት ቀን ሥራ ይሠራል፤ ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር (ያህዌ) የተቀደሰ የዕረፍት ሰንበት ነው፤ በሰንበት ቀን ማንም ቢሠራ በሞት መቀጣት አለበት።" (ዘፀአት 31:15 NASV)

- "የተመረጡ የእግዚአብሔር (ያህዌ) በዓላት ብላችሁ በተወሰኑላቸው ጊዜያት የምታውጇቸው የተቀደሱ ጉባኤዎች እነዚህ ናቸው፤" (ዘሌዋውያን 23:4 NASV)

- "የተረፈውንም አሮንና ልጆቹ ይብሉት፤ እርሾ ሳይገባበት በተቀደሰው ስፍራ፣ በመገናኛው ድንኳን ቅጥር ግቢ ውስጥ አደባባዩ ላይ ይብሉት።" (ዘሌዋውያን 6:16 NASV)

- "እርሻው በኢዮቤልዩ በሚለቀቅበት ጊዜ ለእግዚአብሔር (ያህዌ) እንደተሰጠ ዕርሻ ተቈጥሮ ቅዱስና የካህናቱ ንብረት ይሆናል።" (ዘሌዋውያን 27:21 NASV)

- "የአሮን የተቀደሱ ልብሶች ለትውልዶቹ ይሆናሉ፤ ይኸውም በእነርሱ ይቀቡና ክህነትን ይቀበሉ ዘንድ ነው። ካህን በመሆን እርሱን የሚተካውና በመቅደሱ ለማገልገል ወደ መገናኛው ድንኳን የሚመጣው ወንድ ልጅ ሰባት ቀን ይለብሳቸዋል። የክህነቱን አውራ በግ ወስደህ ሥጋውን በተቀደሰ ስፍራ ቀቅለው።

አሮንና ወንዶች ልጆቹ በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ላይ የአውራውን በግ ሥጋና በሌማት ያለውን ዳቦ ይብሉ። ለክህነታቸውና ለመቀደሳቸው ማስተስረያ የሆኑትን እነዚህን መሥዋዕቶችን ይብሉ፤ የተቀደሱ ስለሆኑ ሌላ ማንም አይብላቸው።" (ዘፀአት 29:29-33 NASV)

& "እነዚህን በቀማሚ እንደ ተሠራ እንደሚሸት ቅመም የተቀደሰ ቅብዐ ዘይት አድርግ፤ የተቀደሰ ቅብዐ ዘይት ይሆናል፤" (ዘፀአት 30:25 NASV)

& "ቅብዐ ዘይቱን ወስደህ ማደሪያውንና በውስጡ ያለውን ሁሉ ቅባ፤ እርሱንና ዕቃውን ሁሉ ቀድስ፤ የተቀደሰም ይሆናል። ከዚያም የሚቃጠል መሥዋዕት መሠዊያውንና ዕቃዎቹን ሁሉ ቅባ፤ መሠዊያውን ቀድስ እጅግም የተቀደሰ ይሆናል። የመታጠቢያው ሰንና ማስቀመጫውን ቅባ፤ ቀድሳቸውም።" (ዘፀአት 40:9-11 NASV)

& "ከዕርሻ ምርትም ሆነ ከዛፍ ፍሬ፣ ማንኛውም ከምድሪቱ የሚገኝ ዐሥራት የእግዚአብሔር (ያህዌ) ነው፤ ለእግዚአብሔርም (ያህዌ) የተቀደሰ ነው።" (ዘሌዋውያን 27:30 NASV)

& "ከእናንተ አንዳንዶቻችሁ እንደዚህ ነበራችሁ፤ አሁን ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና በአምላካችን መንፈስ ታጥባችኋል፤ ተቀድሳችኋል፤ ጸድቃችኋል።" (1 ቆሮንቶስ 6:11 NASV)

**ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ቅድስና ሦስት ዋና ዋና ገጽታዎች አሉት።**

1. **ስፍራዊ ቅድስና፦** በእግዚአብሔር አሠራር በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም አማካይነት የተፈጸመ መቀደስ ነው። ይኼ ቅድስና በአማኙ ዕለታዊ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ስላልሆነ የተሰጠውን ሥፍራ ፈጽሞ ሊያሳጣው አይችልም። ይህ ማለት ስፍራዊ ቅድስና በክርስቶስ ስንሆን ከእኛ ምንም ሳይፈለግ አንድ ጊዜ ለዘላለም አግኝተነዋል ማለት ነው።

& "በዚህ ፈቃድ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ አማካይነት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በቀረበው መሥዋዕት ተቀድሰናል። ... ምክንያቱም በአንዱ መሥዋዕት እነዚያን የሚቀደሱትን ለዘላለም ፍጹማን አድርጎአቸዋል።" (ዕብራውያን 10፡10፤ 14 NASV)

& "በፊቱ ቅዱሳንና ነውር አልባ እንድንሆን ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ በእርሱ መርጦናልና። በፍቅር፣" (ኤፌሶን 1:4 NASV)

በክርስቶስ ሆኖ እጅግ ለደከመውም ሆነ እጅግ ለበረታው እኩል ነው። ምክንያቱም ይኼ ቅድስና የሚወሰነው በክርስቶስ ባገኘነው ስፍራና ጥምረት ብቻ እንጂ በእኛ ድካም እና ብርታት አይደለምና።

& "በመካከላችሁ የዝሙት ርኩሰት እንዳለ በርግጥ ይወራል፤ እንዲህ ያለው ርኩሰት በአረማውያን ዘንድ እንኳ ታይቶ የማይታወቅ ነው፤ የአባቱን ሚስት ያገባ ሰው አለና። ደግሞም ታብያችኋል! ይልቅስ ሐዘን ተሰምቶአችሁ፣ ይህን ድርጊት የፈጸመውን ሰው ከመካከላችሁ ልታስወግዱት አይገባምን?" (1 ቆሮንቶስ 5:1-2 NASV)

& "ከመካከላችሁ አንድ ሰው ከሌላው ጋር ሙግት ቢኖረው፣ ጉዳዩን በቅዱሳን ፊት በማቅረብ ፈንታ እንዴት ደፍሮ በማያምኑ ሰዎች ፊት ለመፋረድ ያቀርባል? ቅዱሳን በዓለም ላይ እንደሚፈርዱ አታውቁምን? በዓለም ላይ የምትፈርዱ ከሆነ፣ እንግዲያው፣ በትንሹ ነገር ላይ ለመፍረድ አትበቁምን?

በምድራዊ ሕይወት ጉዳይ ቀርቶ፣ በመላእክት ላይ እንኳ እንደምንፈርድ አታውቁምን? እንግዲህ እንዲህ ያለ ጉዳይ ሲያጋጥ ማችሁ፣ በቤተ ክርስቲያን የተናቁትን ሰዎች ፈራጅ አድርጋችሁ ሹሙ! ይህንንም የምለው ላሳፍራችሁ ብዬ ነው። ለመሆኑ ከመካካላችሁ ወንድሞችን ለማስታረቅ የሚበቃ አስተዋይ ሰው የለምን? ነገር ግን ወንድም ወንድሙን ለመክሰስ ፍርድ ቤት ይሄዳል፤ ያውም በማያምኑ ሰዎች ፊት! እንግዲህ በመካከላችሁ መካሰስ መኖሩ ራሱ ውድቀታችሁን ያሳያል። ብትበደሉ አይሻልምን? ብትታለሉስ አይሻልምን? እናንተ ግን ራሳችሁ ትበድላላችሁ፤ ታታልላላችሁም፤ ያውምኮ ወንድሞቻችሁን።" (1 ቆሮንቶስ 6:1-8 NASV)

& "ከእናንተ አንዳንዶቻችሁ እንደዚህ ነበራችሁ፤ አሁን ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና በአምላካችን መንፈስ ታጥባችኋል፤ ተቀድሳችኋል፤ ጸድቃችኋል።" (1 ቆሮንቶስ 6:11 NASV)

2. **የምንለማመደው ቅድስና፦** አዲስ ኪዳን ውስጥ ሁለተኛው የቅድስና ገጽታ ሲሆን ከአማኙ ልምምድ ጋር ያዛምደዋል። ይህ የልምምድ ቅድስና በክርስቶስ ካለን ስፍራ ጋር የሚገናኝ አይደለም። በምንኖርበት መንደር እና በምንሠራበት ቦታ ሁሉ የሚገለጥ ነው።

ይኼ የልምምድ ቅድስና በሚከተሉት ነገሮች ላይ ባለን ደረጃ መጠን ሊደገፍ ይችላል።

1) ለእግዚአብሔር ባለን መሰጠት

& "አሁን ግን ከኀጢአት ነጻ ወጥታችሁ የእግዚአብሔር ባሮች ሆናችኋል፤ የምትሰበስቡትም ፍሬ ወደ ቅድስና ያመራል፤ መጨረሻውም የዘላለም ሕይወት ነው።" (ሮሜ 6:22 NASV)

& "እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ ሰውነታችሁን ቅዱስና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕያው መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፤ ይህም እንደ ባለ አእምሮ የምታቀርቡት አምልኮአችሁ ነው።" (ሮሜ 12:1 NASV)

2) አግባብ ካልሆኑ ነገሮች በመለየት

& "ከማያምኑ ሰዎች ጋር አግባብ ባልሆነ መንገድ አትጠመዱ፤ ጽድቅ ከዐመፅ ጋር ምን ግንኙነት አለው? ብርሃንስ ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው? ክርስቶስ ከቤልሆር ጋር ምን ስምምነት አለው? የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ኅብረት አለው? የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ከጣዖታት ጋር ምን ስምምነት አለው? እኛኮ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነን፤ እግዚአብሔርም እንዲህ ሲል ተናግሮአል፤ ከእነርሱ ጋር እኖራለሁ፤ በመካከላቸውም እመላለሳለሁ፤ አምላካቸው እሆናለሁ፤ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ። ስለዚህ ከመካከላቸው ውጡ፤ ለእኔም የተለያችሁ ሁኑ፤ ይላል ጌታ። ርኩስ የሆነውን ነገር አትንኩ፤ እኔም እቀበላችኋለሁ። እኔ አባት እሆናችኋለሁ፤ እናንተም ወንዶችና ሴቶች ልጆቼ ትሆናላችሁ፤ ይላል ሁሉን የሚችል ጌታ።" (2 ቆሮንቶስ 6:14-18 NASV)

& "ከማናቸውም ዐይነት ክፉ ነገር ራቁ።" (1 ተሰሎንቄ 5:22 NASV)

በክርስቶስ ውስጥ ባለን ስፍራና ማንነት ፍጽምናን አግኝተናል። ሆኖም አሁን ባለንበት ምድራዊ ምልልሳችን ሁኔታ ውስጥ በዚህ ፍጽምና ሙላት ልክ ገና አልኖርንም። ዋናው ጉዳይ ግን መኖር የምንችል መሆናችን ነው። ምክንያቱም ሐዋርያው ጴጥሮስ በመልዕክቱ እንዲህ ይለናልና።

& "በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን እርሱን በማወቅ ለሕይወትና ለእውነተኛ መንፈሳዊነት የሚያስፈልገንን ሁሉ የመለኮቱ ኀይል ሰጥቶናል።" (2 ጴጥሮስ 1:3 NASV)

ገና ያልተቀበልነው ልንቀበለው ወይም ልናገኘው የሚገባን አንዳች ነገር የለም። በክርስቶስ ውስጥ ሁሉ ነገር አለንና የሚጎለን አንዳች ነገር የለም። በክርስቶስ ሙሉ ተደርገናል! ስለዚህ ከእኛ የሚጠበቀው እንዴት አድርገን መጠቀም እንዲሁም መመላለስ እንዳለብን ማወቅ ብቻ ነው።

& "የመለኮት ሙላት ሁሉ በአካል በእርሱ ይኖራልና፤ እናንተም የገዥነትና የሥልጣን ሁሉ ራስ በሆነው በክርስቶስ ሙሉ ሆናችኋል።" (ቈላስይስ 2:9-10 NASV)

3. **ፍፁማዊ ቅድስና፦** ከመጨረሻው ፍጹምነት ጋር የተያያዘና ወደ ክብር በምንለወጥበት ወቅት የምናገኘው ነው። ይኼ ማለት ፍጹም እንከን የለሽ መሆን ማለት ነው።

& "እርሱ ብቻ ሳይሆን፣ የመጀመሪያውን የመንፈስ ፍሬ ያገኘን እኛ ራሳችን የሰውነታችን ቤዛ የሆነውን ልጅነታችንን በናፍቆት እየተጠባበቅን በውስጣችን እንቃትታለን።" (ሮሜ 8:23 NASV)

& "እኛ ግን አገራችን በሰማይ ነው፤ ከዚያ የሚመጣውንም አዳኝ፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በናፍቆት እንጠባበቃለን፤ እርሱም ሁሉን ለራሱ ባስገዛበት ኀይል፣ ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል።" (ፊልጵስዩስ 3:20-21 NASV)

& "የሰላም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ መንፈሳችሁ፣ ነፍሳችሁና ሥጋችሁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ ያለ ነቀፋ ይጠበቁ። የጠራችሁ የታመነ ነው፤ እርሱም ያደርገዋል።" (1 ተሰሎንቄ 5:23-24 NASV)

**ለ. የመዳን እና የመቀደስ መንገድ አንድ ነው!**

ሐዋርያው ጳውሎስ የመዳንን እና የመቀደስን መንገድ አንድ እንጂ ሁለት አያደርገውም። በቆላስይስ ምዕራፍ 2 ያለው መሠረታዊ አስተሳሰብ በሕይወታችን ውስጥ የምንመላለስበት መንገድ እርሱ ብቻ ለመዳን እና ለመቀደስ ብቸኛው መንገድ እንደሆነ ነው። ለመዳን አንድ መንገድ እና ለመቀደስ ሌላ መንገድ የለም፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻውን የሁለቱም መንገድ ነው።

& "እንግዲህ ጌታ ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ተቀበላችሁት እንዲሁ በእርሱ ኑሩ፤ በእርሱ ተተክላችሁና ታንጻችሁ፣ እንደ ተማራችሁት በእምነት ጸንታችሁ፣ የተትረፈረፈ ምስጋና እያቀረባችሁ ኑሩ። በክርስቶስ ላይ ሳይሆን፣ በሰዎች ልማድና በዚህ ዓለም መሠረታዊ ሕግጋት ላይ በተመሠረተ ፍልስፍናና ከንቱ ማግባቢያ ማንም ማርኮ እንዳይወስዳችሁ ተጠንቀቁ።" (ቈላስይስ 2:6-8 NASV)

& "በክርስቶስ ኢየሱስ ለመሆን የበቃችሁት ከእርሱ የተነሣ ነው፤ እርሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበባችን፣ ጽድቃችንና ቅድስናችን፣ ቤዛችንም ሆኖአል።" (1 ቆሮንቶስ 1:30 NASV)

እኛ በክርስቶስ ስላለን ስፍራና ማንነት ጽኑ የሆነ መገለጥ ያስፈልገናል። ምክንያቱም ይህን ማግኘታችን ከስፍራችንና ማንነታችን በመነሣት እንድንኖር እጅግ አድርጎ ይረዳናልና።

ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን መልዕክቱ ለምንለማመደው ቅድስና ቁልፍ የሆነ እውነታን አስቀምጧል።

& "እናንተ ግን ክርስቶስን ያወቃችሁት እንደዚህ ባለ መንገድ አይደለም፤ በርግጥ ስለ እርሱ ሰምታችኋል፤ በኢየሱስም እንዳለው እውነት በእርሱ ተምራችኋል። ቀድሞ ስለ ነበራችሁበት ሕይወትም፣ በሚያታልል ምኞቱ የጎደፈውን አሮጌ ሰውነታችሁን አውልቃችሁ እንድትጥሉ ተምራችኋል፤ ደግሞም በአእምሮአችሁ መንፈስ እንድትታደሱ፣ እውነተኛ በሆነው ጽድቅ እንዲሁም ቅድስና እግዚአብሔርን እንዲመስል የተፈጠረውን አዲሱን ሰው እንድትለብሱ ነው።" (ኤፌሶን 4:20-24 NASV)

ሐዋርያው ጳውሎስ ትክክለኛውን የቅድስናን አስተምህሮ የሚቃወም የሰው ሥርዓትና ትምህርት እንዳለ አጽንዖት ሰጥቶ በቆላስይስ ለሚገኙ ቅዱሳን ይነግራቸዋል። ለምን? ቀላል (ለውጡ ግን ኀይለኛ) ከሆነው ከክርስቶስ መልዕክት በላይ ከፍ አድርገው ከሚናገሩት በራስ ፍላጎት ከሚፈጠር የአምልኮ ስሜት፣ እንዲሁም በዐጉል ትሕትናና ሰውነትን በመጨቆን ከልቅነት ለመቆጣጠር ጥበብ ያለው ከሚመስል ማታለያ፣ ነገር ግን ጥቅም የለሽ ድርጊቶች ከሆኑት እራሳቸውን እንዲጠብቁ መምከር ፈልጓልና።

& "እንግዲህ በምትበሉትም ሆነ በምትጠጡት ወይም በዓልን፣ ወር መባቻንና ሰንበትን በማክበር ነገር ማንም አይፍረድባችሁ፤ እነዚህ ሊመጡ ላሉ ነገሮች ጥላ ናቸውና፤ አካሉ ግን የክርስቶስ ነው። ዐጉል ትሕትናንና የመላእክትን አምልኮ የሚወድ ማንም ሰው እንዳያደናቅፋችሁ ተጠንቀቁ። እንደዚህ ያለ ሰው ስላየው ራእይ ከመጠን በላይ ራሱን እየካበ በሥጋዊ አእምሮው ከንቱ ሐሳብ ተሞልቶ ይታበያል፤ ይህ ሰው፣ አካል ሁሉ በጅማትና በማሰሪያ እየተጋጠመ ምግብንም እየተቀበለ እግዚአብሔር በሚሰጠው ማደግ ከሚያድግበት ራስ ከሆነው ጋር ግንኙነት የለውም። ለዚህ ዓለም መርሕ ከክርስቶስ ጋር ከሞታችሁ ታዲያ ለምን እንደዚህ ዓለም ሰው ለሕጎቹ ተገዥ ትሆናላችሁ? አትያዝ! አትቅመስ! አትንካ! እንደሚሉት ዐይነት፣ እነዚህ ሁሉ በሰው ትእዛዝና ትምህርት ላይ የተመሠረቱ ስለሆኑ በተግባር ላይ ሲውሉ ጠፊ ናቸው። እነዚህ ነገሮች በገዛ ራስ ላይ ከሚፈጥሩት የአምልኮ ስሜት፣ ከዐጉል ትሕትናና ሰውነትን ከመጨቈን አንፃር በርግጥ ጥበብ ያለባቸው ይመስላሉ፤ ነገር ግን የሥጋን ልቅነት ለመቈጣጠር አንዳች ፋይዳ የላቸውም።" (ቈላስይስ 2:16-23 NASV)

የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ውስጥ ዕለት ዕለት መሞት እንዳለብን የሚናገርበት አንድም ቦታ የለም። ይልቁንም ላንዴና ለዘላለም ከክርስቶስ ጋር በእርሱ መስቀል መሞታችንን ይናገራል። አሁን ማድረግ ያለብን ኢየሱስ በመስቀል ላይ የሠራውን በየዕለቱ በማስታወስ እርሱን ይዞ ወይም አምኖ መኖር ብቻ ነው።

& "እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ፣ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ በተቀመጠበት በላይ ያሉ ነገሮችን እሹ፤ አሳባችሁም በላይ ባለው ላይ እንጂ በምድራዊ ነገር ላይ አይሁን። ሞታችኋልና፤ ሕይወታችሁም ከክርስቶስ ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ተሰውሮአልና፤ ሕይወታችሁ የሆነው ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ እናንተም በዚያን ጊዜ ከእርሱ ጋር በክብር ትገለጣላችሁ። ስለዚህ ምድራዊ ምኞቶቻችሁን ግደሉ፤ እነዚህም፦ ዝሙት፣ ርኩሰት፣ ፍትወት፣ ክፉ ምኞትና አምልኮተ ጣዖት የሆነው መጐምጀት ናቸው።" (ቈላስይስ 3:1-5 NASV)

ትኩረታችሁ በምድራዊ ነገሮች ላይ በሆነ መጠን ኑሮአችሁ ከምድራዊ ዓለም በመነሣት ላይ የታነጸ ይሆናል። ትኩረታችሁ በሰማያዊ ዓለም ላይ በሆነ መጠን ደግሞ ሕይወታችሁ ከሰማያዊ ዓለም በመነሣት የምትኖሩት ይሆናል።

በአንድ በኩል የተቀመጥንበትን ሰማያዊ ዓለም በተመለከተ መገለጥን ስናገኝ ወዲያውኑ እውነታው በሕይወታችን ውስጥ ይፈስሳል። በሌላ በኩል ደግሞ በክርስቶስ ውስጥ ስላለን ነገር ንቁ ስንሆን በምድራዊ

የአሁን ሁኔታችን ወስደን እንጠቀምበታለን።

ሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክቱን የጻፈላቸው በቆላስይስ የሚገኙት በክርስቶስ የሆኑት ቅዱሳን በዚያን ጊዜ የሞቱት ከምን አንጻር ነው? በሥጋም ሆነ በመንፈስ ሙታን እንዳልነበሩ ግልጽ ነው። እርሱ እያላቸው ያለው ከዚህ በፊት ከአሮጌው ሕይወት ጋር ያላችሁ ትስስር ተቋርጧል፣ እናም አሁን እውነተኛ ሕይወታችሁ በክርስቶስ በእግዚአብሔር ዘንድ ተሰውሮአል ነው። አሮጌው ሕይወታችን አክትሞአል፣ ከክርስቶስ ጋር በእግዚአብሔር የተሰወረ አዲስ መንፈሳዊ ሕይወት አግኝተናል።

## ሐ. ሕጉ በክርስቶስ ለሆነው የሕይወታችን መመሪያ አይደለም።

ለአይሁድ የተሰጡት 613 ሕግጋት በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት ያመች ዘንድ ሊቃውንት የሥነምግባር ሕግ (Moral Law)፣ የሥርአት ሕግ (Ceremorial Law) እና የፍትሐብሔር ሕግ (Civil Law) በማለት በሦስት ዋና ዋና ምድቦች ይከፍሏቸዋል።

በሐዋርያው ጳውሎስ አነጋገር በክርስቶስ የሆኑት ቅዱሳን ለተወሰኑ ሕጎች የሚሰማቸው ፍላጎት በራሱ በክርስቶስ ካለው ሕይወት እየሳተ ነው።

& "ለዚህ ዓለም መርሕ ከክርስቶስ ጋር ከሞታችሁ ታዲያ ለምን እንደዚህ ዓለም ሰው ለሕጎቹ ተገዥ ትሆናላችሁ? አትያዝ! አትቅመስ! አትንካ!" እንደሚሉት ዐይነት፣ እነዚህ ሁሉ በሰው ትእዛዝና ትምህርት ላይ የተመሠረቱ ስለሆኑ በተግባር ላይ ሲውሉ ጠፊ ናቸው።" (ቈላስይስ 2:20-22 NASV)

ሕጉ በክርስቲያናዊ ሕይወታችን መመሪያ የማይሆን ከሆነ፣ የቅድስና ኑሮን ለመኖር እንዴት እንችል ይሆን? ለመቀደስ ቁልፎቹስ ምንድን ናቸው?

& "ስለዚህ ምድራዊ ምኞቶቻችሁን ግደሉ፤ እነዚህም፦ ዝሙት፣ ርኵሰት፣ ፍትወት፣ ክፉ ምኞትና አምልኮተ ጣዖት የሆነው መጐምጀት ናቸው። በእነዚህም ምክንያት የእግዚአብሔር ቍጣ በማይታዘዙት ላይ ይመጣል፤ እናንተም ቀድሞ በኖራችሁበት ሕይወት በእነዚህ ትመላለሱ ነበር፤" (ቈላስይስ 3:5-7 NASV)

በዚህ ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ አንዳንድ ነገሮችን እንድንገድል እና ሌሎች ነገሮችን እንድናስወግድ አዞናል ወይም መመሪያ ሰጥቶናል። ኢየሱስ ክርስቶስ በእነዚህ ድርጊቶች ውስጥ በአንዱም የሚራመድበት ምንም መንገድ የለም፣ ስለሆነም ከእሱ ጋር የምንለይ ከሆነ እኛም በእነሱ ውስጥ አንሄድም።

ሐዋርያው ጳውሎስ "በምድር ያሉትን ብልቶቻችሁን ግደሉ" ሲል እየተናገረ ያለው የአካል ክፍሎቻችንን በተመለከተ አይደለም። እሱ እየተናገረ ያለው ለሁሉም ዓይነት የጾታ ርኩሰት እና ሌሎች ድርጊቶች እንደሞተ ሰው መኖር አለባችሁ እያለ ነው።

& "አሁን ግን ቍጣን፣ ንዴትን፣ ስድብን፣ ሐሜትንና አሳፋሪ ንግግርን የመሳሰሉትንም ሁሉ አስወግዱ፤ አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር አውልቃችሁ ስለ ጣላችሁ እርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ።" (ቈላስይስ 3:8-9 NASV)

አንደበትን መቆጣጠር እና የግል ጸባይን መግራት አስፈላጊ ነው። ይህ ተግባር በምድር እስካለን ድረስ አንዴ ብቻ የሚከሰት ሳይሆን ሁልጊዜም የሚቀጥል ነው። የዚህ ተግባር ጥቅሙ ከወገኖች (በክርስቶስ ከሆኑት)

ጋር ያለንን ኅብረት በመልካም ሁኔታ ለማስቀጠል እና ለማስጠበቅ ነው።

አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ከእኛ ከተወገደ በኋላ ወገኖችን (በክርስቶስ የሆኑትን) መዋሸት ፍጹም በእኛ ውስጥ ካለው መንፈስ ቅዱስ ጋር የሚፃረር ባህሪይ ነው። የአዲሱን ሰው ማንነት የሚፃረርን ተግባር መፈጸም በግልፅ በክርስቶስ ውስጥ ማን እንደሆንን አለማወቃችንን ያሳያል።

**መ. ጸጋ የመለወጥ አቅም ነው!**

በጸጋው (በኢየሱስ ክርስቶስ) የለወጥ አቅም ከመደገፍ ይልቅ ሰውን ለመለወጥ የራሳችንን ሰዋዊ የስነምግባር ትምህርት ቀርጸን ሰውን ለመለወጥ መታገል የለብንም። ይልቁንም እኛ ማድረግ ያለብን ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ በማለት የተናገረውን ነው።

& "እኛም እያንዳንዱን ሰው በክርስቶስ ፍጹም አድርገን ማቅረብ እንችል ዘንድ፣ ሰውን ሁሉ በጥበብ ሁሉ እየመከርንና እያስተማርን እርሱን እንሰብካለን፤" (ቈላስይስ 1:28 NASV)

ብዙዎቻችን ጸጋን የምንረዳው ድነት የሚገኝበት ብቻ አድርገን ነው። እውነታው ግን ጸጋ ስኬታማ የሆነ (መኖር የሚያስችል) ተግባራዊ አስተማሪም ነው። ስለዚህ የጸጋውን ትክክለኛ ትምህርት ለመስማት ከመዘግየት ይልቅ ያለማቋረጥ በትኩረት መስማት አለብን።

& "ድነት የሚገኝበት የእግዚአብሔር ጸጋ ለሰዎች ሁሉ ተገልጦአልና፤ ይህም ጸጋ በኀጢአት መኖርንና ዓለማዊ ምኞትን ክደን፣ በአሁኑ ዘመን ራሳችንን በመግዛት በጽድቅ፣ በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት እንድንኖር ያስተምረናል፤ ይህም የተባረከ ተስፋችን የሆነውን የታላቁን የአምላካችንንና የአዳኛችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ በመጠባበቅ ነው፤ እርሱም ከክፋት ሊቤዠን መልካም የሆነውን ለማድረግ የሚተጋውን የእርሱ የሆነውን ሕዝብ ለራሱ ያነጻ ዘንድ ራሱን ስለ እኛ ሰጥቶአል። እንግዲህ ልታስተምር የሚገባህ እነዚህን ነው፤ በሙሉ ሥልጣን ምከር፤ ገሥጽም፤ ማንም አይናቅህ።" (ቲቶ 2:11-15 NASV)

ያው እኛን የሚያድነን ጸጋ፣ በዚህ ዓለም ውስጥ እግዚአብሔርን በመምሰል እንድንኖር ያስተምረናል። ይህ ጸጋ ለኀጢአት ፈቃድን በመስጠት ወደ ዓለማዊነት አኗኗር ይመራል የሚለው ንግግር ባለማወቅ የሚነገር ሐይማኖታዊ አስተሳሰብ መሆኑን ያሳያል። ሐዋርያው ጳውሎስ በግልጽ እንደተናገረው ሰዎች ኀጢአትን ለማድረግ ጸጋ አያስፈልጋቸውም፣ ይልቁንም ጸጋ የእግዚአብሔር የኀጢአት መድኃኒት ነው።

ጸጋ ለኀጢአት ፈቃድን በመስጠት ወደ ዓለማዊነት አኗኗር ይመራል ብሎ መፍራት በፍጹም ከጸጋው ተቃራኒው ነው። ስለዚህ ቃሉ ከአስተያየቶቻችን ወይም ከፍርሃቶቻችን የበለጠ ስልጣን ሊኖረው ይገባል።

በኀጢአት ልምምድ ትግል ውስጥ ያሉ ሰዎች ስለ ጸጋ መስማት ያለባቸው በትንሹ አይደለም፤ አብዝተው መስማት አለባቸው። ለምን? ኀጢአት የእግዚአብሔርን ጸጋ የማያስቆመው ሲሆን የእግዚአብሔር ጸጋ ግን ኀጢአትን ያስቆመዋል። ደግሞም በሕይወታችን ከማይገቡ ድርጊቶች ጋር ትግል ላይ ያለን ሰዎች ማድረግ ያለብን ነጻ ለመሆን በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ ማሰላሰል እና የሚረዳንን ጸጋ መቀበል ነው።

& "ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች ስላልሆናችሁ፣ ኀጢአት አይገዛችሁምና። እንግዲህ ምን ይሁን? ከሕግ በታች ሳይሆን፣ ከጸጋ በታች በመሆናችን ኀጢአት እንሥራን? በጭራሽ አይገባም!" (ሮሜ

6:14-15 NASV)

& "እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበልና በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ፣ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ።" (ዕብራውያን 4:16 NASV)

ጸጋ ያስተምረናል!! እንዴት ድንቅ መምህር ነው። በአሮጌው ቃል ኪዳን ውስጥ "የሕግ ቁጥጥር" ባልተሳካበት ሥፍራ ጸጋ ይሳካል።

"ስለዚህ በእምነት እንጸድቅ ዘንድ ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያደርሰን ሞግዚታችን ሆነ። አሁን ግን ያ እምነት ስለ መጣ፣ ከእንግዲህ በሕግ ሞግዚትነት ሥር አይደለንም።" (ገላትያ 3:24-25 NASV)

ለሕጉ የማይቻል ምን ነበር? እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ አደረገው!

& "ስለዚህ በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉት አሁን ኵነኔ የለባቸውም፤ ምክንያቱም የሕይወት መንፈስ ሕግ በክርስቶስ ኢየሱስ ከኀጢአትና ከሞት ሕግ ነጻ አውጥቶአችኋል። ሕግ ከሥጋ ባሕርይ የተነሣ ደክሞ ሊፈጽም ያልቻለውን፣ እግዚአብሔር የገዛ ልጁን በኀጢአተኛ ሰው አምሳል፣ የኀጢአት መሥዋዕት እንዲሆን በመላክ ፈጸመው፤ በዚህም ኀጢአትን በሥጋ ኰነነ፤ ይኸውም በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ በምንመላለስ በእኛ፣ ሕጉ የሚጠይቀው ጽድቅ ሙሉ በሙሉ እንዲፈጸም ነው።" (ሮሜ 8:1-4 NASV)

ሐዋርያው ጳውሎስ "የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ" ሲል መዳናችሁን ፍጹም አድርጉት፣ እንዳታጡት ጠብቁት እያለ ሳይሆን ከውስጥ ወደ ውጪ በአኗኗራችሁ (በሕይወት ምልልሳችሁ) ግለጡት እያለ ነው። በራሳችን ጥረት ትግል ውስጥ እንዳንገባ መፍትሔውንም አብሮ አስቀምጦልናል።

& "ስለዚህ፣ ወዳጆቼ ሆይ፤ ሁልጊዜም ታዛዦች እንደ ነበራችሁ ሁሉ፣ አሁንም እኔ በአተገባችሁ ሳለሁ ብቻ ሳይሆን፣ ይልቁንም አሁን በሌለሁበት ጊዜ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ፤ እንደ በጎ ፈቃዱ መፈለግንና ማድረግን በእናንተ ውስጥ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና።" (ፊልጵስዩስ 2፡12-13)

የምንሰናከለው እይታችንን ከኢየሱስ (የእምነታችን ጀማሪ እና ፈጻሚ ከሆነው) ስንቀይር ብቻ ነው።

& "የእምነታችን ጀማሪና ፍጹም አድራጊ የሆነውን ኢየሱስን እንመልከት፤ እርሱ በፊቱ ስላለው ደስታ መስቀሉን ታግሦ፣ የመስቀሉንም ውርደት ንቆ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአል።" (ዕብራውያን 12:2 NASV)

ስለዚህ በኀጢአት ሥራ የሚቀጥል አማኝ በመካድ ውስጥ እየኖረ ነው። የኢየሱስ ግልጽ መገለጥ ስለሌለው በማንነት ቀውስ እየተሰቃየ ነው። ማንነቱንና መልኩንም ረስቷል።

& "ቃሉን የሚሰማ፣ ነገር ግን የሚለውን የማይፈጽም ሰው ፊቱን በመስተዋት እንደሚያይ ሰው ነው፤ ራሱንም አይቶ ይሄዳል፤ ወዲያውም ምን እንደሚመስል ይረሳል፤" (ያዕቆብ 1፡23-24 NASV)

አንድ አማኝ ከመውደቅ ጋር ሲታገል የማንነት ቀውስ ውስጥ ነው። የኢየሱስን (ጸጋ) የማያቋርጥ መገለጥ ያስፈልገዋል፣ ምክንያቱም እውነተኛ ማንነቱን የሚገልጠው ያ ነውና።

& "እኛም ሁላችን ባልተሸፈነ ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያንጸባረቅን፣ የእርሱን መልክ እንድንመስል ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን፤ ይህም የሚሆነው መንፈስ ከሆነ ጌታ ነው።" (2ኛ ቆሮንቶስ 3፡18 NASV)

በመጋቢ አለማየሁ ገመቹ ተዘጋጀ

በዕትመት መልክ አዘጋጅቶ ለሽያጭ ማዋል የተከለከለ ነው!

ነሐሴ 21/2014 ዓ.ም